# ኢሕአፓ በሂውስተን ቴክሳስ የተሳካ ሕዝባዊ ስብሰባ አጠናቀቀ

ይህ በኢሕአፓ ድጋፍ ኮሚቴ ጥሪ በነሃሴ ፳፮ (Aug. 26, 06) ከምሺቱ 6፤ 00 ሰዓት እስከ 10፤30 የተካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ የተዋጣለት ካደረጉት አብይ ጉዳዮች መሀከል ተስብሳቢው ኢሕአፓን የመሰለ ቀዳሚና መሪ ድርጅት በተለይ አሁን  ኢትዮጵያ በምትገኝበት አሳሳቢና አስጊ ወቅት በኮሚኒቲያችን መሀከል ተገኝቶ አንገብጋቢ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ገለጻ ማድረጉን  በጉጉት የጠበቀው መሆኑን ከማሳየቱም ሌላ ከሂወስተንም ሆነ ከአጎራባች ከተሞች ከማንኛውም ጊዜ በተለየ በየኮሚኒቲያቸው ውስጥ ጎላ ያለ መሕበራዊ ሚና ሊኖራቸው የሚችሉትን በበለጠ በማካተቱም ጭምር ነው ፡፡

የዕለቱ እንግዳ ተናጋሪዎች ሁለቱ የኢሕአፓ የከፍተኛ አመራር አባላት ኢትዮጵያ አሁን ያለቸበትን የወገን ያለህ የሚያሰኝ የኢኮኖሚ ድቀት የማሕበራዊ ደዌና የፖለቲካ ዝቅጠት በሰፊው ካስጨበጡ በኋላ በአጠቃለይ ምን መደረግ አለብት? ለሚለው የወቅቱ ጥያቄ አገር የማዳን ጥያቄ እንደሆነ በመያሻማ አቀራረብ አስረድተዋል፡፡  በጥያቄም ሆነ በአስተያየት መልክ በተሰብሳቢው የተንፀባረቁት ሀሳቦች ባጠቃላይ ኢሕአፓን ደጋፊና አበረታች የነብሩ ከመሆናቸውም ሌላ ያልተንዛዙ  አቢይ በሆኑ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ መሆናቸው በተለይ ስብሰባውን ደማቅና ኢሕአፓ መሰል ስብሰባዎችን እንዲያዘወትር ጠቋሚ ስሜትን አንፀባር'ቀዋል፡፡ ከሶስቱም ከተሞች ኢትዮጵያዊያን ለድርጅቱ አርዳታ የሚውሉ የመግቢያ ቲኬቶቾን አስቀድሞ በመግዛትም  ከፍተኛ ትብብርን አሳይተዋል፡፡

በሂውስት ኢሕአፓ ድጋፍ ኮሚቴ